## አምላክ አትተወኝ

አምላክ አትተወኝ

የእጆችህ ሥራ ነኝ/2/

ቀኑን ሁሉ ወደ አንተ እጮኻለሁ

ዕረፍትም አላገኝ አንተን አወራለሁ

ቀድሞ አባቶቻችን በአንተ ስላመኑ

ታድናቸው ነበር ቆመው ሲለምኑ

አዝ . . . . . .

መከራ ደርሶብኝ በስቃይ ጊዜ

ጠላቶች ከበውኝ ደርሶብኝ አባዜ

እንደ ባሳን ኮርማ በዙሪያዬ ሆነው

እንደ አገሣ አንበሳ አፋቸውን ከፍተው

አዝ . . . . . .

ጉልበቴ ደከመ እንደ ውኃ ፈሰሰ

ልቤም ቀለጠብኝ ኃይሌ ተደቆሰ

በትቢያ ላይ ስወድቅ ችላ አትበለኝ

በከበቡኝ ጊዜ ውሾች ጥለውኝ

አዝ . . . . . .

ነፍስና ስጋዬን ከውሾች ታደጋት

ፈጽሞ ችላ አትበል እኔን ከመራዳት

ከአንበሳ መንጋጋ ከተዋጊ በሬ

ከክፉ አድነኝ ከጨካኙ አውሬ